# በጊንጪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ አፋቸውን በኦሮምኛ ቋንቋ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ያላቸው የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የውጤት ተዛምዶ

በላቸው ማንደፍሮ[1]

**አጠቃሎ፤** *የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ በሚያደርጉት የክፍል ውስጥ ተሳትፎና በአማርኛ ቋንቋ ውጤታቸው መካከል ያለውን ተዛምዶ መመርመር ነው። ይህን ዓላማ ለማሳካት ተዛምዷዊ የጥናት ንድፍን ተግባራዊ ተደርጓል። የጥናቱ ተሳታፊዎች በጊንጪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተማሩ 48 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ከ48 ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ያላቸውን ተሳትፎ በምልከታና በጽሑፍ መጠይቅ እንዲሁም የአማርኛ ቋንቋ ውጤታቸውን ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ተሰብስቧል። የተሰበሰቡ መረጃዎች ጥናቱ ይዟቸው የተነሳውን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ፣ የቀላል ድህረታዊ እና የነጻ ናሙና ቲቴስት ስሌቶች አማካይነት የተሰበሰቡ መረጃዎች ተተንትነዋል። በትንተናው ውጤትም በአማርኛ ቋንቋ ክፍለጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ እና በአማርኛ ቋንቋ ውጤት መካከል ጉልህ የሆነ አዎንታዊ ተዛምዶ (r=.642፣ P<.01፣ ባለሁለት ጫፍ) እንዳለ እና የተዛምዶ ደረጃውም ከፍተኛ እንደሆነ የፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ፍተሻው አሳይቷል። ነጻ ተለዋዋጩ (በአማርኛ ቋንቋ ክፍለጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ) ጥገኛ ተለዋዋጩን (የአማርኛ ቋንቋ ውጤትን) 41.2% እንደሚገልጸው የቀላል ድህረታዊ ትንታኔው ውጤት ($R^2$ = .412፣ β = .642፣ F (1፣ 47) = 32.267፣ t = 5.680፣ p = .000) አሳይቷል። የወንድና የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ አማካይ ውጤቶች መካከል ልዩነት አለመኖሩን የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ትንታኔው (t (46) = .776, p = 0.442) ያሳዩ ሲሆን የአማርኛ ቋንቋ ውጤታቸው መካከል ያለውን ልዩነት ተፈትሾ የሴትና የወንድ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት (t (46) = .301, p = .765) አለመኖሩን በጥናቱ ተረጋግጧል። ከጥናቱ ግኝት በመነሳት መምህራን የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ እንዲጨምር የበኩላቸውን አስተዋጽዖ ቢያበረክቱ የሚሉና ሌሎች አስተያየቶች በአጥኚው ቀርበዋል።*

***ቁልፍ ቃላት፤*** *የክፍል ውስጥ ተሳትፎ እና የትምህርት ውጤት*

## መግቢያ

የቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የተፋጠነና የተቀላጠፈ ይሆን ዘንድ ተማሪዎች በንቃት እንዲሳተፉ ማድረግ ተገቢነት አለው። በተለይም በአሁኑ ዘመን የአሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴ

[1] በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛን ማስተማር (TeAm) መርኃግብር የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪ

የሚሰጠው ትኩረት እየጨመረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የተማሪዎች ተሳትፎ በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚበረታታ ተግባር ነው (Tudor, 1993)፡፡ ለዚህም የመምህራን የተለያዩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር በተማሪዎች ተሳትፎ ላይ ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ ውጤት አለው (Richards, 2001)፡፡ Borich (2004) የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማሳደግ መምህራን በክፍል ውስጥ ለገለፃ የሚያጠፉትን ረዥም ጊዜ በመቀነስ ተማሪዎች ሊሳተፉበት የሚያስችላቸውን ሰፊ የመወያያ ጊዜ መስጠትና በተግባሩ እንዲሳተፉ በማድረግ የመማር ማስተማር ስራውን ውጤታማ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

የቋንቋ መምህሩ ሚና በክፍል ዉስጥ የመማር ማስተማሩን ሁኔታ ማመቻቸት ነዉ፡፡ ይህም ተማሪዎች ድጋፍ በሚፈልጉበት ሁኔታ ነፃ ሆነዉ እንዲቀርቡ፣ የሚያዉቁትን ነገር ቋንቋዉን ተጠቅመው በተለያዩ አዉዶች መግለጽ እንዲችሉና በአጠቃላይ ጥሩ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያበረታታ ሁኔታን መፍጠር ነዉ፡፡ Borich (2004) እንደሚገልጹት በመማር ሂደት የተማሪዉ ተሳትፎ ቁልፍ ሚና አለው፡፡ የትምህርት ተሳትፎ መገለጫውም ተማሪዎች ለተለየዩ የትምህርት ዓይነቶች ራሳቸዉን በመስጠት ምን ያህል ሰዓታትን እንደሚጠቀሙ የሚያሳይ ነዉ፡፡ የተማሪዎች ዉጤታማነት ወይም ስኬታማነት ደረጃ የሚያሳየዉ ተማሪዎች ጥያቄዎችንና የተለያዩ የትምህርት ስራዎችን የመረዳትና በትክክል መስራታቸውን ነው፡፡

የክፍል ዉስጥ ጥያቄዎች በስፋት በጥቅም ላይ የሚውሉ የማስተማርያ ስልቶች ናቸው፡፡ Hamilton & Bradyን (1991) ጠቅሰው Eggen & kauchak (2013) እንደሚያስረዱት በክፍል ዉስጥ በመምህራን ተደጋግመው የሚቀርቡ ጥያቄዎች ከተማሪዎች ውጤት ጋር አዎንታዊ ዝምድና አላቸው፡፡ በተመሳሳይ ኤርሚያስ (1996) በትምህርት ሰዓት በክፍል ውስጥ ተማሪዎች የሚኖራቸዉ ተሳትፎ ለውጤታቸዉ የሚኖረዉ አስተዋጾ ከክፍል ዉጪ በጥናት ስልት ከሚያሳልፉት ጊዜ እኩል ክብደት እንዳለው አስረድተዋል፡፡ እንደ አብዛኛዎቹ የትምህርት ተሃድሶ ንድፈ ሐሳቦች ጥሩ የማስተማር ሥራ ሁልዜዜ ተማሪዎችን ለትምህርት የሚያነሳሳ፣ በክፍል ውስጥም እንዲሳተፉ የሚያደርግና የትምህርት ዉጤትንም የሚያሳድግ ነው፡፡

በአንጻሩ የትምህርት ተሳትፎ ብቻ ለውጤት መሳካት ምክንያት አይደለም የሚሉ ተመራማሪዎችም አሉ፡፡ Marx & Marion (1977) ትምህርቱ ህይወታዊና አስደሳች እንዲሆን ተማሪው በመማር-ማስተማሩ ሂደት በክፍል ዉስጥ መሳተፍ እንዳለበት ገልጸው ተሳትፎው በራሱ ውጤት የሚያመጣ እንዳልሆነ ይሞግታሉ፡፡ ይህም በመማር ማስተማሩ ሂደት ካለው ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ጥቂት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ያላቸው ከፍተኛ

ውጤት ሆኖ በክፍል ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ግን እንብዛም ሊሆን ይችላል፡፡ በአንጻሩ በክፍል ውስጥ ጥሩ ተሳትፎ ኖሯቸው በፈተና ወቅት የሚያስመዘግቡት ውጤት ግን አመርቂ ላይሆን ይችላል፡፡ ይህን መሞገቻ ነጥብ በማንሳት የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከውጤት ጋር ተዛምዶ የለውም የሚል ድምዳሜ ላይ የሚደርሱ አሉ፡፡ ይህንኑ መነሻ ሀሳብ Meior & Nicols (1978) የውጤት መለያየቱ በውጤታቸው ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ከሚችሉ ተላውጦዎች (የመምህሩ ልምድና ብቃት፣ የመማሪያ ዐውድ፣ የፈተናው ደረጃ፣ ወዘተ.) አንጻርም መታየት ስለሚኖርበት የ Marx & Marionን (1977) የምርምር ግኝት እንደማይቀበሉት ይጠቁማሉ፡፡ ይህም የተለያዩ አመለካከት በጥናት መረጋገጥ እንዳለበት የሚያመላክት ነው፡፡

በበርካታ ጥናቶች ግን ያላቸው ተዛምዶ የላቀ እንደሆነ Kauchak & paul (1993) እንደሚያስረዱት በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡት ተማሪዎች በትምህርት ተሳትፏቸው ከ75% እና ከዚያ በላይ እንደ ሆኑና ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የትምህርት ተሳትፎ 50% እና ከዚያ በታች እንደ ሆነ ነው፡፡ Everston, et al. (1980) እና Fredrik (1977) ይህም የትምህርት ተሳትፎ በውጤት ላይ ምን ያህል ተጽእኖ እንዳለው በመግለጽ የKauchak & paul (1993)ን ሀሳብ ያጠናክራሉ፡፡

McGeeal (1985) የክፍል ዉስጥ የትምህርት ጊዜ ከተሳትፎና ከዉጤት ጋር የተያያዘ እንደሆነና ተማሪዎች ብዙ በተሳተፉ ጊዜ ውጤታቸዉ እየጨመረ እንደሚሄድ በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡ በMcGeeal (1985) ጥናት እንደ ተረጋገጠዉ በጥያቄና መልስ ክፍለ ጊዜያት በንቃት የሚሳተፉ ተማሪዎች 80% ዉጤታማ እንደሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም Slavin (2018) የተሻለ ስኬት ማግኘት ተማሪዎች የበለጠ እንዲሰሩና እንዲበረታቱ እንደሚያደርግ ይጠቁማሉ፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎች ብዙ በተሳተፉ ቁጥር ውጤታቸውም የዚያኑ ያህል ከፍ እንዲል ሊያደርግ ይችላል፡፡

Amidon (1976) በአንድ ክፍል ዉስጥ ሰፋ ባለ የጥያቄና መልስ ሂደት የሚሳተፉ ተማሪዎች በመጠኑ ከሚሳተፉ ተማሪዎች የበለጠ የመቀበል ችሎታ እንዳላቸው፣ ዉጤታቸዉም የተሻለ እንደ ሆነ በጥናታቸው አረጋግጧል፡፡ በተመሳሳይ Tony (1987) እንደገለጹት ተማሪዎች በውጤት የተሻሉ ተማሪዎች ለመሆን በመማሩ ሂደት ንቁ ተሳታፊና በሚሰጣቸዉ ሥራ ላይ ዉጤታማ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ የክፍል ዉስጥ ሂደት መምህሩንና ተማሪዉን የሚያሳትፍ በመሆኑ ተማሪዎችም ይህም ሂደት እንዲሟላ የሚጠበቅባቸዉን ነገር ማከናወን አለባቸው፡፡

Stevenson & Joy (1994) እንደገለጹት አንዳንድ ተማሪዎች ምናልባት ጥረትና ችሎታ ቀጥተኛ ዝምድና አላቸዉ ወደሚለው አመለካከት ሊመጡ ይችላሉ። እና ዉጤት ከፍተኛ የሆነ ጥረትና ተሳትፎን ይጠይቃል። ይህ ማለት ደግሞ ተማሪዉ ችሎታ ያንሰዋል ማለት አይደለም። በመሆኑም የትምህርት ተሞክሮ የተማሪዎችን በብቃት ላይ ያላቸዉን አመለካከት ሊለዉጠዉ ይችላል ማለት ነዉ።

መምህራን አንድ ማወቅ ያለባቸው ነገር የተማሪው የመማር ስልት ከመምህራን የማስተማር ስልት ጋር ሁልጊዜ በትይዩ ላይሄድ ይችላል። አንዳንድ ጊዜ እንዲውም አንዱ ከሌላው የተለየ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ጥቂት ተማሪዎች ዝምታን በመምረጥ ለመማር ማዳመጥ ይመርጣሉ። ነገር ግን መምህራን በመናገር ይማራሉ ብለው ያምናሉ። ከዚያም በክፍል ውስጥ የጥቂት ተማሪዎች የሚታይ ቃላዊ ግንኙነት ደረጃ ከራሳቸው አመለካከት ጋር የተገናኘ ሊሆን ይችላል። ይህም በተሻለ ሁኔታ ጋር በተወሰነ መልኩ ደግሞ ተማሪዎች ለመናገር ይፈልጉ ይሆናል፤ ግን ይህን ለማድረግ ደግሞ ይፈራሉ። ይህም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በተማሪዎቹ የትምህርት ውጤት ላይ አዎንታዊ ሆነ አሉታዊ ተጽእኖ አለው። skinner (1985) የተማሪዎች ባሕሪ፣ ስብእና የተለያዩ ተግባራት፣ የአከባቢ ሁኔታና የመሳሰሉት ጉዳዮች በተማሪው ውጤት ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ ይገልጻል።

ሆኖም ግን ቀደም ብሎ እንደተገለጸው በሁለቱ ተለዋዋጮች መካከል ያለዉ ተዛምዶ ብዙ ጊዜ ጥያቄ ሲፈጥርና ሲያወዛግብ ይታያል። ለዚህም በውጭ ሀገሮች ላይ የተደረጉ ጥናቶች ግኝት ልዩነት ማሳያቱ አስረጂ ይሆናል፤ መለያየቱ ደግሞ ለተጨማሪ ለጥናት የሚጋብዝ ነው። በተለይም ጥናቶቹ በተለያዩ ቋንቋዎችና ሀገሮች ላይ እንደመደረጋቸው በአማርኛ ቋንቋ ያለውን መመርመር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

የዚህ ጥናት አጥኚ ከዚህ ጥናት ጋር የሚዛመዱ ጥናቶችን ለማግኘት ባደረገው አሰሳ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያለ ተሳትፎ ከተማሪዎች ውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ በተመለከተ የተደረገ ጥናት አልገጠመውም። በተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተሳትፎ ላይ ግን በርካታ ምርምሮች በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ተደርገዋል። ከእነዚህም ውስጥ የበላይ (1992)፣ የለዘር (2004) እና የግዛቸው (2014) ጥናቶች ይጠቀሳሉ። በላይ (1992) የ11ኛ ክፍል ሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ምርምር ያደረጉ ሲሆን በጥናታቸው ግኝትም ሴት ተማሪዎች ያላቸው የተሳትፎ መጠን ዝቅ ማለቱን ጠቁመዋል። ለዘር (2004) በተመሳሳይ ጾታ ተኮር የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ጥናት አድርገዋል። ጥናቱ ሴቶች ብቻቸውን የሚማሩባቸው

እና ከወንዶች ጋር ተቀላቅለው ከሚማሩባቸው የግል ትምህርት ቤቶች ላይ ያላቸውን ተሳትፎ በንጽጽር የተጠና ነው፡፡ በጥናቱ ውጤትም ብቻቸውን የሚማሩ ሴት ተማሪዎች ከወንዶች ጋር ተቀላቅለው ከሚማሩት በተሸለ ተሳትፎ እንዳላቸው ተመላክቷል፡፡ ግዛቸው (2014) ደግሞ የተማሪዎች ተሳትፎን ከማስተማሪያ ዘዴዎች ጋር ያለውን ተዛምዶ በሚመለከት ጥናት አድርገዋል፡፡ በጥናታቸው ግኝትም የማስተማሪ ዘዴዎችና የተማሪዎች ተሳትፎ ዝምድና እንዳለው አሳይተዋል፡፡

በዚህ ክፍል የተዳሰሱ ሶስቱም ጥናች በተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ትኩረታቸውን ያድርጉ እንጂ ተሳትፏቸው ከትምህርት ውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ አላጠኑም፡፡ ለዚህ ጥናት መነሻ ከሆኑት ጉዳዮች ውስጥ አንዱም ይህንን ክፍተት ለመሙላት በማቀድ ነው፡፡ በተጨማሪም አጥኚዉ በሥራ ላይ በቆየባቸዉ በርካታ  አመታት በክፍል ዉስጥ በመማር-ማስተማር ሂደት ንቁ ተሳትፎ የሌላቸዉ ብዙ የማይናገሩና የማይሰሩ በትምህርታቸዉ ከፍተኛ ዉጤት ሲያስመዘግቡና አንዳንድ ጊዜም  የተሻለ ተሳትፎ ያላቸዉ ተማሪዎች በትምህርት ዝቅተኛ ዉጤት ሲያገኙ ተመልክቷል፡፡ ከሌሎች መምህራንም በዚሁ ጉዳይ ላይ ተመሳሳይ መረጃዎችን አግኝቷል፡፡ ይህም በጥናቱ ዳራ ላይ የተለያዩ የመስኩ ምሁራን የገለጹት ሀሳብ (የተማሪዎች ተሳትፎ ከውጤታቸው ጋር ተዛምዶ መኖር) ጋር የሚጋጭ ልምድ ነው፡፡ ለዚህም ጥናት እንደሚያስፈልገው አጥኚው ስላመነ ለማጥናት ተነሳስቷል፡፡ በተጨማሪም በበላይ (1992)፣ በለዘር (2004) እና በግዛቸው (2014) ጥናቶች ከሴት ተማሪዎች ይልቅ የወንድ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፏቸው ዝቅ ያለ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ ከአጥኚው ተሞክሮ አንጻር ይህ የጥናት ግኝት በአሁኑ ዘመን ካለው ጾታን መሰረት ያደረገ ተሳትፎ አንጻር የተቃረነ ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ይህንንም መነሻ ሀሳብ በጥናት ማረጋገጥ ስላስፈለገ ለአጥኚው መነሻ ሆኖታል፡፡

## የምርምሩ መሰረታዊ ጥያቄዎች

በዚህ ጥናት ምላሽ እንዲፈለግላቸው የታሰቡት መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፤ በኦሮምኛ ቋንቋ አፊ-ፊት ሆነው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች

1. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የክፍል ዉስጥ ተሳትፎ ከውጤት ጋር ተዛምዶ አለው?

2. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያላቸው ተሳትፎ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤትን የመተንበይ ድርሻ ምን ምን ያህል ነው?

3. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያላቸው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በጾታ ልዩነት ያሳያልን?

## የአጠናን ዘዴ

ጥናቱ በአይነቱ መጠናዊ ሲሆን ገላጭ ተዛምዷዊ ንድፍን በመከተል ተከናውኗል፡፡ በመሆኑም ለጥናቱ የተሰበሰቡት መረጃዎች በተዛምዶ መለኪያ ስታትስቲክስ ተተንትነው በተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎና በትምህርት ውጤታቸው መካከል ያለው ተዛምዶ ተፈትሿል፡፡

## የጥናቱ ተሳታፊዎች

ለዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት የተመረጠው ትምህርት ቤት በኦሮምያ ክልል፣ በምዕራብ ሸዋ ዞን በደንዲ ወረዳ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህር ቤቶች መካከል የጊንጪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ የተመረጠው በአመች የንሞና ስልት ነው፡፡ አመች የንሞና ስልት ተግባራዊ የተደረገበት ምክንያት አጥኚዉ ከሚሰራበት ቦታ በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኝና ለመረጃ አሰባሰቡ የተሻለ አመቺ ሁኔታ ይኖራል በሚል መነሻ ነው፡፡

ጥናቱ የሚመለከታቸው በ2015 ዓ.ም ትምህርታቸውን እየተከታተሉ የሚገኙ ተማሪዎች ብዛት 51 ነው፡፡ የሚማሩት በአንድ መማሪያ ክፍል ብቻ ነው፡፡ ሁሉም ተማሪዎች ለጥናቱ ስለሚያስፈልጉና ንሞና ለመውሰድ የሚያስገድድ ባለመሆኑ በጠቅላይ የንሞና ዘዴ (Comparehensive Sampling) መሰረት በሙሉ ተማሪዎች ለጥናቱ ይወሰዳሉ፡፡

### የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

ለዚህም የተመረጡት አግባብነት ያላቸው ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በክፍል ዉስጥ በአጥኚው የሚደረግ የተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ ምልከታ፣ የጽሑፍ መጠይቅ እና የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ናቸው፡፡

## የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ምልከታ

Benneft & Namara (1979) የምልከታ መርሀግብሮች ለበርካታ ዓላማዎች ጥቅም ላይ እንደሚውሉ በመግለጽ ከነዚህም አንዱ በክፍል ዉስጥ ባሉ ተግባራትና በተማሪው ውጤት መካከል ያለውን ግንኙነት ለመመርመር ነው ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ በተመሳሳይ BLaws & H-Doorlag (2011) የመማሪያ ክፍልን ባህርይና የጥናት ክህሎትን ለማጥናትና መረጃ ለመሰብሰብ እጅግ አስፈላጊ የሆነ ዘዴ ምልከታ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ በዚህ መነሻነት ይህ ጥናትም በክፍል ውስጥ ያለውን የተማሪዎች ተሳትፎ ለመመርመር የክፍል ውስጥ ምልከታን ተጠቅሟል፡፡ በተጨማሪ ምልከታ የተመረጠበት ምክንያት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሲሳተፉ (ጥያቄ በመጠየቅ፣ ምላሽ በመስጠት፣ የክፍል ሥራ በመስራት፣ ወዘተ.) ተግባራዊ የሚሆንና ሊታይ የሚችል በመሆኑ ለዚህ ጥናት የተዋቀረ ወይም የተደራጀ ምልከታ (Structured Observation) ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ጥናቱ በሚካሄድበት ጊዜ ስምንት ክፍለ ጊዜዎችን ለመረጃ መሰብሰብያነት ተጠቅሟል፡፡

የተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ ምልከታ የተካሄደዉ በክለሳ ድርሳናት ላይ በተዳሰሱ ንድፈ ሀሳባዊ ተግባራት አማካይነት ነው፡፡ የትምህርት ተሳትፎ የተማሪዎች በክፍል ውስጥ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ጥያቄ የመጠየቅና ከመምህሩ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠትን የግልና የቡድን ሥራን መስራትን ያጠቃልላል፡፡ የክፍል ዉስጥ የትምህርት ተሳትፎ በአንድ አጥኚ በምልከታ በክፍል ዉስጥ በማንኛዉም ጊዜ የሚከናወኑ ድርጊቶችን ለምሳሌ (/) በመጠቀም መረጃውን ሊሰበስብ ይችላል (David, 1985)፡፡ አጥኚው በስራ ላይ ያዋለውም ይህንኑ ዘዴ ነው (የተዘጋጀው የምልከታ ቅጽ ከአባሪ 2 ይመልከቱ)፡፡

## የጽሑፍ መጠይቅ

የጽሑፍ መጠይቁ የተዘጋጅበት ዓላማ የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በሚመለከት ከተተኳሪ ተማሪዎች መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ የተዘጋጀውም በአጥኚው ሲሆን እንደመነሻ የሆኑት በምዕራፍ ሁለት ላይ የተዳሰሱ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መለኪያዎች ናቸው፡፡ በውስጡም የተካተቱበት የጥያቄዎች ብዛት 22 ሲሆኑ ሁሉም የሊክርት ስኬልን መሰረት አድርገው ተዘጋጅተዋል፡፡ 22 ጥያቄዎች በአራት ምድብ የተከፈሉ ሲሆን በምድቦቹ ውስጥ የተካተቱ ጥያቄዎች ብዛት በጥያቄና በአስተያየት መልኩ የሚታዩ 5 ጥያቄዎች፣ በጥንድ ወይም በቡድን ውይይት መልኩ የሚታዩ 6 ጥያቄዎች፣ የክፍል ተግባራት ላይ ያለ ተሳትፎን

የሚመለከቱ 6 ጥያቄዎች እና በጽብረቃ (Presentation) መልኩ የሚታዩ 5 ጥያቄዎች ናቸው (የተዘጋጀው መጠይቅ ከአባሪ 1 ይመልከቱ)፡፡

የመጠይቁን ትክክለኛነት ለመፈተሽ በጥናቱ አማካሪና የክፍል ደረጃውን በሚያስተምሩ መምህራን ታይቶ አስተያየት የተሰጠበት ሲሆን አስተማማኝነቱን ለመፈተሽ ደግሞ የክፍል ደረጃቸው በሚመሳሰሉ በሀጫሉ የሁለተኛ ደረጃ 30 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የፍተሻ ጥናት (Pilot Study) ተደርጓል (በፍተሻ ጥናቱ የተሰበሰበው መረጃ ከአባሪ 5 ይመልከቱ)፡፡ ከዚያም በሙከራ ጥናቱ የተገኘው ውጤት በክሮንባኽ አልፋ ስሌት ተሰልቶ α = 946 ሆኗል (የስሌቱ ዝርዝር መረጃ ከአባሪ 8 ላይ ይመልከቱ)፡፡ ይህም ከ.7 በላይ በመሆኑ መጠይቁ ለዋናው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ አገልግሏል፡፡

## የአማርኛ ቋንቋ ፈተና

የአማርኛ ቋንቋ ፈተና የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ውጤት ለመፈተሽ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ የተማሪዎችን ውጤት በሰነድ ፍተሻ ከተማሪዎች የውጤት ማጠራቀሚያ ቋት መሰብሰብ ይቻል ነበር፡፡ ግን በፈተና ጥያቄዎች የክብደትና የቅለት ደረጃ፣ የመለየት ብቃት፣ የአስተማማኝነትና የይዘት ተገቢነት ችግሮች አንጻር ሊመጡ የሚችሉ ውጫዊ ተጽዕኖዎችን ለመቆጣጠር ፈተናው በአጥኚው ተዘጋጅቶ ቢፈተኑ ተመራጭ ይሆናል ተብሎ ስለታመነበት ነው፡፡

ፈተናው የተዘጋጀው በአጥኚው ሲሆን ተተኳሪ ተማሪዎች ፈተናውን የተፈተኑት በየካቲት ወር ላይ በመሆኑ የመጀመሪያው ወሰነትምህርት ወቅት በመርሀ ትምህርቱና በመማሪያ መጽሐፉ መሰረት ሁሉም የትምህርት ይዘቶችና የትምህርት ልምዶች እንደተሰጣቸው የክብደት ደረጃ ታይቶ ተዘጋጅቷል፡፡ ፈተናው ከመዘጋጀቱ በፊት የጥያቄ ማውጫ ቢጋር (Item Spesfication) ቀድሞ ተዘጋጅቷል፡፡ ከዚያም ትክክለኛነቱን ለመፈተሽ በሚያስተምሩት መምህራንና በጥናቱ አማካሪ በማሳየት የይዘትም ይሁን የቋንቋ እርማት ተሰጥቶታል፡፡ በዚህም የፈተናውን ትክክለኛነት ከፍ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡

የፈተናውን አስተማማኝነት፣ የቅለትና ክብደት ደረጃ እና የመለየት ብቃት እና አስተማማኝነት ለመፈተሽ ሀጫሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የፍተሻ ጥናት (Pilot Study) ተደርጓል፡፡ በሙከራ ጥናቱ 30 ተማሪዎች የተዘጋጀውን ፈተና

ተፈትነዋል፡፡ ፈተናው ቁርጠኛ ምላሽ የሚሰጠው በመሆኑ በአጥኚው ታርሞ በውጤት መመዝገቢያ ሰንጠረዥ ላይ ተመዝግቧል (በሙከራ ጥናቱ ወቅት የተሰበሰበው መረጃ ከአባሪ 6 ይመልከቱ)፡፡ ከዚያም የጥያቄዎች የክብደትና ቅለት ደረጃ (Level of Difficulty) ተለይቷል፡፡ በዚህም መሰረት 2 ቀላል (0.77 እና በላይ)፣ ቀሪዎቹ 48 ጥያቄዎች መካከለኛ ክብደት (ከ0.40 እስከ 0.76) ሆነው በመገኘታቸው ከቀላል እስከመካከለኛ ጥያቄዎች እንደተካተቱ አመልክቷል (የእያንዳንዱ ጥያቄ የክብደት ደረጃ ከአባሪ 7 ይመልከቱ)፡፡

የጥያቄዎች የመለየት ብቃት (Item Discrimination) በሙከራ ጥናቱ ወቅት ከ30 ተማሪዎች በተሰበሰበው መረጃ ተሰልቷል፡፡ በስሌቱ መሰረት የተገኘው ውጤት ሁሉም ጥያቄዎች የመለየት ብቃት ከ0.33 እስከ 0.78 ባለው ተገኝቷል፡፡ ይህም ውጤት የበለጠ ወደ1 እየቀረበ የሚሄድ በመሆኑ የጥያቄዎች የመለየት ብቃት ከመካከለኛ እስከከፍተኛ እንደሆነ አሳይቷል (የእያንዳንዱ ጥያቄዎች የመለየት ብቃት ከአባሪ 7 ይመልከቱ)፡፡ አስተማማኝነቱን ለመፈተሽ ደግሞ በክሮንባኽ አልፋ ተሰልቶ $\alpha = .923$ ውጤት ተገኝቷል (የፍተሻ ጥናቱ አስተማማኝነት ዝርዝር ስሌት ከአባሪ 9 ይመልከቱ)፡፡ ይህም ከፍተኛ አስተማማኝነት እንዳለው ስለሚያመለክት ለዋናው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ አገልግሏል፡፡

## የመረጃ አተናተን ዘዴ

በመረጃ አሰባሰብ ሂደቶች (3.5) እንደተገለጸው በትምህርት ተሳትፎና በትምህርት ውጤት መካከል ያለውን ተዛምዶ ለመመርመር በመጀመሪያ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች እና በመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ተደምረው የተገኘው ውጤት የተማሪዎችን የክፍል ተሳትፎ እንዲሁም የአማርኛ ቋንቋ ተፈትነው ያገኙት ውጤት የአማርኛ ቋንቋ ውጤትን እንዲወስን ተደርጎ ውጤቱ በጥንቃቄ ተሞልቷል፡፡ በአሞላል ወቅት ስህተት እንዳይፈጠር ሁለት መምህራን የተሞላውን ውጤት በትክክል ስለመሞላቱ አረጋግጠዋል፡፡ ከዚያም የተሞላው መረጃ SPSS Version 26 መተግበሪያ የፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ (Pearson Correlation Cofficient)፣ የቀላል ድህረት (Simple Linear Regression) እና የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት (Indipendant Samples T-Test) ተተንትኗል፡፡

በትምህርት ተሳትፏቸው እና በትምህርት ውጤታቸው መካከል ያለው ተዛምዶ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ስሌቱ የተካሄደውም ስለሁለቱ ተላውጦዎች በተገኙት ውጤቶች ውስጥ ፍንግጥ ነጥቦች እንደሌሉ በባለሳጥን

ግራፎች (Boxplots) ተሰርተው (አባሪ 15 ይመልከቱ) ከተፈተሹ በኋላ ነበር። በተጨማሪ ሁለቱ ተላውጦዎች ያላቸው ግንኙነት በብትን ግራፍ (Scatterplot) ተሰርቶ አንጻራዊ በሆነ ዕይታ ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳላቸው (አባሪ 17 ይመልከቱ) ከታወቀ በኋላ ነበር።

የተማሪዎች በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ያላቸው ተሳትፎ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤትን ከመተንበይ አኳያ ያለውን ድርሻ ለማወቅ የቀላል ድህረት (Simple Linear Regression) ትንተና ተካሂዷል። ለዚህ ስሌትም ተንባይ ተለዋዋጩ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ያለ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ሆኖ ሲወሰድ ተተንባይ ተለዋዋጩ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ሆኖ የቀላል ድህረት ስሌቱ ተሰልቷል። የተንባይ ተለዋዋጩ ድርሻም ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ በተጋርቶት መጠን መለኪያ (Coefficient of Determination-$R^2$) ተፈትሿል። የተንባይ ተጽእኖውን ጥንካሬ ለማወቅም መደበኛ ድህረታዊ መጣኝ (Standardized Regeration Coefficient- β) ተግባራዊ ተደርጓል።

የቀላል ድህረት ስሌት ከመከናወኑ በፊትም እሙኖቹ መሟላታቸውን የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል። የመጀመሪያው እሙን የናሙና መጠን ሲሆን Pituch & Stevens (2016:123) ለማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍ ጥናት ለእያንዳንዱ ተንባይ (ነጻ) ተላውጦ 15 የናሙና መጠን በቂ እንደሆነ በገለጹት መሰረት አንድ ተንባይ ያለው ይህ ጥናት 48 የናሙና መጠንን መሰረት አድርጎ መሰራቱ እሙኑ እንዳልተጣሰ አመላካች ነው። ሌላው እሙን በተላውጦዎቹ መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት (Linearity) መኖሩን ማረጋገጥ ሲሆን ተንባይ ተላውጦ የሆነው የተማሪዎች የአማርኛ ክፍለጊዜ ተሳትፎ ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ጋር ያላቸው ተዛምዶ 0.642 ያህል ዝምድና ስላሳየ እሙኑ መሟላቱ ተረጋግጧል።

የስህተት መጠን ስርጭት (Homoscedasticity) እሙን መሟላቱን ለመፈተሽ ቀሬ ውጤቶቹ (standardised residual) በብትን ግራፍ ላይ በz-Predicted እና በz-residual መካከል ባለ ግንኙነት ተፈትሿል። በአባሪ 18 እንደተመላከተው የስህተት መጠኖች አንድ ላይ የተከማቹ ባለመሆናቸውና አንጻራዊ በሆነ እይታ ተበትነው የሚታዩ በመሆናቸው እሙኑ እንደተሟላ መረዳት ተችሏል። ከዚህም ሌላ በተካሄደው የስርጭት ወጥነት ፍተሻ (Tests of Normality) የአማርኛ ትምህርት ፈተናው ውጤት የሾጣጣነት መጠን የዜድ (Z value for the Skewness) ዋጋ 0.985፤ የዝብጠት መጠን የዜድ (Z value for Kurtosis) ዋጋ ደግሞ -0.798፤ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ውጤት የሾጣጣነት መጠን የዜድ ዋጋ 1.92፣ የዝብጠት መጠን የዜድ ዋጋ -1.42፤ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት የሾጣጣነት መጠን የዜድ ዋጋ

1.725፣ የዝብጠት መጠን የዜድ ዋጋ -0.391 ሆነው ተገኝተዋል (አባሪ 12 ይመልከቱ)። እነዚህ የሸጣጣነትና የዝብጠት የዜድ ዋጋዎች ደግሞ መጠናቸው ±1.96 (P< 0.05) ርቀት ውስጥ የሚካተቱ በመሆናቸው ውጤቶቹ ወጥ ስርጭት እንዳላቸው አመልክተዋል። በዚህ መልኩ ሁሉም እሙኖች እና መደበኛ ሥርጭት መሟላታቸው በመረጋገጡ የመረጃ ትንተናው ፓራሜትራዊ ቴስት በሆነው በድህረት ትንተና ተተንትኗል።

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያላቸው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በጾታ ልዩነት ማሳየት አለማሳየታቸውን ለመፈተሽ የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት ተደርጓል። የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ከመሰላቱ በፊት የሴትና የወንድ የአማርኛ ትምህርት መረጃዎችና የክፍል ውስጥ መረጃዎች የቲ-ቴስት ዋና እሙን የሆነውን መደበኛ ስርጭት (Normal Distribution) ማሟላታቸው በሻፒሮ-ዊልክ አማካይነት ተፈትሿል። በሻፒሮ-ዊልክ የተፈተሸበት ምክንያትም በእያንዳንዱ ቡድን (ሴትና ወንድ) ያሉት ተጠኝዎች ብዛት ከ50 በታች በመሆኑ ነው። የወንድ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ውጤት እንዲሁም የወንድና የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ውጤት መረጃዎች የሻፒሮ-ዊልክ ፍተሻ ውጤት P>0.05 ሆኗል። በመሆኑም ሶስቱም መረጃዎች በሻፒሮ-ዊልክ ፍተሻ እሙኑን እንዳሟሉ ለማወቅ ተችሏል። ሆኖም ግን የሴት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ውጤት መረጃዎች በሻፒሮ-ዊልክ ፍተሻ ግን እሙኑን አሟልተው ባለመገኘታቸው (P<0.05) የበለጠ ፍተሻ እንደሚያስፈልግ ለመረዳት ተችሏል። በዚህም መሰረት በግድለት (skewness) እና በዝብጠት (Kurtosis) መደበኛ ውጤቶች አማካይነት ተጨማሪ ፍተሻ ተካሂዶባቸዋል። የግድለት (1.519) እና የዝብጠት (- .749) መደበኛ ውጤቶቹም በ-1.96 እና በ1.96 መካከል በመገኘታቸው እሙኑ መሟላቱን ለመረዳት ተችሏል (የመደበኛ ስርጭት ፍተሻ ውጤቶቹ ከአባሪ 13 እና ከአባሪ 14 ተመልቷል)። በተጨማሪም የነጻ ናሙና ስሌቱ የተካሄደውም በሴትና በወንድ ቡድኖች በተገኙት ውጤቶች ውስጥ ፍንግጥ ነጥቦች እንደሌሉ በባለሳጥን ግራፎች (Boxplots) ተሰርተው (አባሪ 16 ይመልከቱ) ከተፈተሹ በኋላ ነበር። መረጃዎቹ የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት መሰረታዊ እሙን የሆነውን የስርጭት ወጥነት እንደሚያሟሉ በተገለጸው መንገድ ከተፈተሹ በኋላ በነጻ ናሙና ስሌት ተተንትነዋል።

## የውጤት ትንተናና የውጤት ማብራሪያ

### የውጤት ትንተና

የጥናቱ የመጀመሪያ ጥያቄ "በኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ሆነው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የክፍል ዉስጥ ተሳትፎ ከውጤት

ጋር ተዛምዶ አለው?" የሚል ሲሆን የተማሪዎች ተሳትፎ በምልከታ በተማሪዎች መጠይቅ፣ የተማሪዎች ውጤት ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ ፈተና የተሰበሰቡ መረጃዎች በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ትንታኔው በሰንጠረዥ 4.1 ተደራጅቶ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 1፤ የተተኳሪ ተማሪዎች ተሳትፎና ውጤት ተዛምዶ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ**

| ተላውጦ (Variable) | የናሙና ብዛት (No.) | አማካይ ውጤት (Mean) | መደበኛ ልይይት (SD) | ተዛምዶ (Pearson Correlation) | | ጉልህነት (Sig. (2-tailed)) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የክፍል ውስጥ ተሳትፎ | የትምህርት ውጤት | |
| የክፍል ውስጥ ተሳትፎ | 48 | 64.63 | 30.53 | 1 | .642** | .000 |
| የትምህርት ውጤት | 48 | 30.38 | 8.34 | .642** | 1 | .000 |

**ጉልህ ተዛምዶ በ0.01 ደረጃ (ባለ 2-ጫፍ)

በሰንጠረዥ 4.1 እንደተመላከተው ተተኳሪ 48 ተማሪዎች ተሳትፎና ውጤት ተዛምዶ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት r=.642፣ P<.01 (ባለሁለት ጫፍ) ነው፡፡ ይህም በሁለቱ ተላውጦዎች (በተተኳሪ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የትምህርት ውጤት) መካከል ጉልህ አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳለ ያሳያል፡፡ መጠኑ ደግሞ መካከለኛ እንደሆነ Dornyei (2007) እና ያለው (2009) ባስቀመጡት መስፈርት አማካይነት መረዳት ተችሏል፡፡ የተዛምዶው መጠንና አቅጣጫ የተለየው በፒርሰን ተዛምዶ ተሰልቶ የተገኘውን ውጤት (ከ 0 እስከ -1/+1) Dornyei (2007) እና ያለው (2009) ባቀረቧቸው መስፈርቶች መሰረት ነው፡፡ በመሆኑም ተዛምዶው አዎንታዊ ቁጥር ማስመዝገቡ ተዛምዶው አዎንታዊ መሆኑን ሲያመለክት የተዛምዶው መጠን ደግሞ ከፍተኛ እንደሆነ እና ይህም ውጤት በስታትስቲክስ ጉልህ (P<.01) መሆኑን የትንተናው ውጤት ያሳያል፡፡

የጥናቱ ሁለተኛ ጥያቄ "በኦሮምኛ ቋንቋ አፊ-ፊት ሆነው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያላቸው ተሳትፎ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤትን የመተንበይ ድርሻ ምን ምን ያህል ነው?" የሚል ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት መረጃዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎን በምልከታና በመጠይቅ የአማርኛ ቋንቋ ውጤትን በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ተሰብስበው በቀላል ድህረት (Simple Linear Regression) ትንተና ተተንትኗል፡፡ የትንታኔው ውጤት በሰንረዥ 4.2 ይመልከቱ፡፡

**ሰንጠረዥ 2፤ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የአማርኛ ቋንቋ ውጤትን የመተንበይ ድርሻ፣ በቀላል ድህረት**

| ተላውጦዎች | የተጋርቶ መጠን ($R^2$) | ድህረታዊ መጣኝ (B) | መደበኛ ስህተት (Standard Error) | መደበኛ ድህረታዊ መጣኝ (β) | የቲ-ዋጋ (t) | ጉልህነት (sig.) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ኢተለዋዋጭ (Constant) | .412 | 19.034 | 2.204 | | 8.636 | .000 |
| የክፍል ውስጥ ተሳትፎ | | .175 | .031 | .642 | 5.680 | .000 |

ተንባይ ተላውጦ፤ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ
ተተንባይ ተላውጦ፤ የትምህርት ውጤት

በሰንጠረዥ 4.2 እንደተመላከተው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን የመተንበይ ድርሻ ለመፈተሽ በተደረገው ትንተና በአማርኛ ክፍለ ጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ($R^2$ = .412፣ β = .642፣ F (1፣ 47) = 32.267፣ t = 5.680፣ p = .000) አዎንታዊ የላቀ የመተንበይ ድርሻ እንዳለውና የመተንበይ ድርሻው በስታትስቲክስ ጉልህ መሆኑን ያሳያል፡፡ የትንበያ ውጤቱ በአማርኛ ቋንቋ ውጤት ላይ ያለው ልዩነት (variance) 41.2% ($R^2$ = .412) ያህሉ በበአማርኛ ቋንቋ ትምህር በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ሊገለጽ እንደሚችል የሚያሳይ አንድምታ አለው፡፡ ነጻ ተላውጦው በአማርኛ ቋንቋ ውጤት ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ለመመርመር በመደበኛ ድህረታዊ መጣኝ ስሌት ተሰልቷል፡፡ የድህረታዊ መጣኝ ስሌቱ እንደሚያሳየው በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ (ነጻ ተለዋዋጩ) በአንድ

አሀድ መጨመር የአማርኛ ቋንቋ ውጤት ላይ በ.175 ያሀል እንዲጨምር ያደርገዋል የሚል አንድምታ ይሰጣል፡፡ ይህም ውጤት በስታቲክስ ጉልህ እንደሆነ (p = .000) ያሳያል፡፡

የጥናቱ ሶስተኛ ጥያቄ "በኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ሆነው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያላቸው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በጾታ ልዩነት ያሳያልን?" የሚል ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘትም በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ያለን የክፍል ውስጥ ተሳትፎን በምልከታና በተማሪዎች መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ እና የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ውጤት ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ተሰብስቦ በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት (Indipendant Sample T-Test) ተተንትኗል፡፡ በመጀመሪያ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ቀጥሎም የአማርኛ ቋንቋ ውጤት እንደየቅደም ተከተላቸው ቀርበዋል፡፡ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የጾታ ልዩነት በሰንጠረዥ 4.3 ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 3፤ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ጾታን መሰረት ያደረጉ አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት**

| ተላውጦ (Variable) | ጾታ (sex) | ብዛት (n) | አማካይ ውጤት (Mean) | መደበኛ ልይይት (SD) | የነጻነት ደረጃ (df) | የቲ-ዋጋ (t) | ጉልህነት (sig.) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የክፍል ውስጥ ተሳትፎ | ሴት | 25 | 67.92 | 33.634 | 46 | .776 | .442 |
| | ወንድ | 23 | 61.04 | 27.055 | | | |

በሰንጠረዥ 4.3 እንደተመላከተው የ25 ሴት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ክፍለጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ አማካይ ውጤት 67.92 ሲሆን የ23 ወንድ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ውጤት ደግሞ 61.04 ነው፡፡ ይህም የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ አማካይ ውጤት ከወንድ ተማሪዎች ተሳትፎ አማካይ ውጤት በ6.88 ውጤት እንደሚበልጥ ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ መደበኛ ልይይት ከወንድ ተማሪዎች መደበኛ ልይይት በ6.579 ይበልጣል፡፡ በሁለቱ ቡድኖች (በሴትና በወንድ) መካከል ጉልህነት መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽም በተደረገው የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት የተገኘው ውጤት t (46) = .776, p = 0.442 ሆኗል፡፡ ይህም ውጤት P>0.05 በመሆኑ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ስታትስቲካዊ

ልዩነት አለመኖሩን ያመለክታል። በመሆኑም የሴትና የወንድ ተማሪዎች የክፍል ተሳትፎ ተመጣጣኝ እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል።

**ሰንጠረዥ 4.4፤ የአማርኛ ቋንቋ ጾታን መሰረት ያደረጉ አማካይ ውጤቶች ንጽጽር በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት**

| ተላውጦ (Variable) | ጾታ (sex) | ብዛት (n) | አማካይ ውጤት (Mean) | መደበኛ ልይይት (SD) | የነጻነት ደረጃ (df) | የቲ-ዋጋ (t) | ጉልህነት (sig.) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የአማርኛ ትምህርት ውጤት | ሴት | 25 | 30.72 | 9.977 | 46 | .301 | .765 |
| | ወንድ | 23 | 30.00 | 6.317 | | | |

በሰንጠረዥ 4.4 እንደተመላከተው የ25 ሴት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ አማካይ ውጤት 30.72 ሲሆን የ23 ወንድ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ አማካይ ውጤት ደግሞ 30.00 ነው። ይህም የሴት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ፈተና አማካይ ውጤት ከወንድ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ አማካይ ውጤት በ0.72 ውጤት እንደሚበልጥ ያሳያል። በተመሳሳይ የሴት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መደበኛ ልይይት ከወንድ ተማሪዎች መደበኛ ልይይት በ3.66 ይበልጣል። በሁለቱ ቡድኖች (በሴትና በወንድ) የአማርኛ ቋንቋ አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህነት መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽም በተደረገው የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት የተገኘው ውጤት $t(46) = .301$, $p = .765$ ሆኗል። ይህም ውጤት $P>0.05$ በመሆኑ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ስታትስቲካዊ ልዩነት አለመኖሩን ያመለክታል። በመሆኑም የሴትና የወንድ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ውጤት ተመጣጣኝ እንደሆኑ ለማወቅ ተችሏል።

## የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ በሚያደርጉት የክፍል ውስጥ ተሳትፎና በአማርኛ ቋንቋ ውጤታቸው መካከል ያለውን ተዛምዶ መመርመር ነው። በውስጡም ሶስት ንዑሳን ዓላማዎችን መርምሯል። ሶስቱንም ንዑሳን ዓላማዎች ለመመርመር የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በክፍል ውስጥ ምልከታ እንዲሁም በተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መፈተሸ የጽሑፍ መጠይቅ

ተሰብስቧል። የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ውጤት ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ ፈተና ተፈትሿል። ከዚያም ፈተናዎቹ በአጥኚው ታርመው የተማሪዎችን ውጤት እንዲወክሉ ከተደረገ በኋላ የምልከታውና የመጠይቁ መረጃ ደግሞ ተደማምሮ የአማርኛ ክፍለ ጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎን እንዲወክል ተደርጎ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ፣ በቀላል ድህረታዊ እና በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትነዋል።

የጥናቱ የመጀመሪያ ንዑስ ዓላማ በኦሮምኛ ቋንቋ አፌ-ፈት ሆነው "አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የሚያደርጉት የክፍል ዉስጥ ተሳትፎ ከዉጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ መመርመር" የሚል ሲሆን ተዛምዷቸውን ለመመርመር የተሰበሰቡ መረጃዎች በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ተተንትነዋል። በትንታኔው ውጤትም በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ያለ የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የአማርኛ ቋንቋ ውጤት ጉልህ የሆነ አዎንታዊ ተዛምዶ (r=.642፣ P<.01 (ባለሁለት ጫፍ)) እንዳላቸው በጥናቱ ተረጋግጧል። የተዛምዶ መጠኑ ደግሞ መካከለኛ እንደሆነ Dornyei (2007) ባስቀመጡት መስፈርት አማካይነት መረዳት ተችሏል።

በአንደኛው ንዑስ ዓላማ የተገኘው የዚህ ጥናት ውጤት Kauchak & paul (1993) ካስረዱት ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡት ተማሪዎች በትምህርት ተሳትፏቸው ከ75% እና ከዚያ በላይ እንደ ሆኑና ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የትምህርት ተሳትፎ 50% እና ከዚያ በታች እንደሆነ ከገለጹት ሀሳብ ጋር የሚቀራረብ ነው። Kauchak & paul (1993) ከገለጻቸው በመነሳት የትምህርት ውጤትና የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ተዛምዶ እንዳላቸው የገለጹ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በአማርኛ ቋንቋ መማር ማስተማር ዐውድም ተመሳሳይ ውጤት እንዳለ የሚያሳይ በመሆኑ ጥናቱ Kauchak & paul (1993) ጋር ተደጋጋሚ ነው። በተመሳሳይ በMcGeeal (1985) ጥናት እንደ ተረጋገጠዉ በጥያቄና መልስ ክፍለ ጊዜያት በንቃት የሚሳተፉ ተማሪዎች 80% ዉጤታማ ከገለጹት እና Slavin (2018) የተሻለ ስኬት ማግኘት ተማሪዎች የበለጠ እንዲሰሩና እንዲበረታቱ እንደሚያደርግ ከጠቆሙት ጋር የዚህ ጥናት ውጤት ይመሳሰላል።

የዚህ ጥናት ሁለተኛ ዓላማ "በኦሮምኛ ቋንቋ አፌ-ፈት ሆነው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያላቸው ተሳትፎ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤትን የመተንበይ ድርሻ ምን ያህል እንደሆነ መፈተሽ" የሚል ነው። ይህን

ዓላማ ለማሳካትም በጽሑፍ መጠይቅ፣ በምልከታና በአማርኛ ቋንቋ ፈተና የተሰበሰቡ መረጃዎች በቀላል ድህረታዊ ተተንትነዋል፡፡ በትንተናው ውጤትም ነጻ ተለዋዋጩ (በአማርኛ ቋንቋ ክፍለጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ) ጥገኛ ተለዋዋጩን (የአማርኛ ቋንቋ ውጤትን) 41.2% እንደሚገልጸው የቀላል ድህረታዊ ትንታኔው ውጤት ($R^2$ = .412፣ β = .642፣ F (1፣ 47) = 32.267፣ t = 5.680፣ p = .000) አሳይቷል፡፡ ይህም የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በአማርኛ ቋንቋ ውጤት መጨመር ወይም መቀነስ ያለው ተጽዕኖ የላቀ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

Stevenson & Joy (1994) በቋንቋ መማር ማስተማር ዐውድ ተሳትፎ ከሌለ የተማሪዎች ውጤትም ሊቀንስ እንደሚችል ከገለጹት ሀሳብ ጋር ይደጋገፋል፡፡ በተመሳሳይ Borich (2004) በመማር ሂደት የተማሪዉ ተሳትፎ ቁልፍ ሚና እንደሚጫወትና ለውጤታቸው ክፍ ማለት ወይም ዝቅ ማለት የሚያበረክተው አስተዋጽዖ የላቀ እንደሆነ ከገለጹት ሀሳብ ጋር የዚህ ጥናት ውጤት ጋር የሚደጋገፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የዚህ ጥናት ሶስተኛ ዓላማ "በኦሮምኛ ቋንቋ አፊ-ፈት ሆነው አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያላቸው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በጾታ ልዩነት መኖር አለመኖሩን መፈተሽ" የሚል ነው፡፡ ለዚህ ዓላማ ምላሽ ለማግኘት በምልከታ፣ በጽሑፍ መጠይቅና በአማርኛ ቋንቋ ፈተና የተሰበሰቡ መረጃዎች የወንድና የሴት ተማሪዎች አማካይ ውጤቶች ለየብቻ ተሰልተው በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትነዋል፡፡ በትንታኔው ውጤትም በጥናቱ ውስጥ የተካተቱ 25 ሴት ተማሪዎች በአማርኛ ክፍለ ጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ አማካይ ውጤት 67.92 ሲሆን የ23 ወንድ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ውጤት ደግሞ 61.04 በመሆኑ የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ አማካይ ውጤት ከወንድ ተማሪዎች ተሳትፎ አማካይ ውጤት በ6.88 ውጤት እንደሚበልጥ ያሳያል፡፡ ይህም ከወንድና ከሴት ተማሪዎች የበለጠ ተሳትፎ ያደረጉት ሴት ተማሪዎች ናቸው የሚያስብል ውጤት ከገላጭ ስታትስቲካዊው መረጃ መረዳት ቢቻልም ይህ ውጤት ስታቲካዊ ጉልህነት መኖር አለመኖሩ በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት መፈተሽ አለበት፡፡ የወንድና የሴት ተማሪዎች አማካይ ውጤቶች በስታቲካዊ ጉልህነታቸው በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተፈትሾ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል የተገኘው አማካይ ውጤት ስታትስቲካዊ ጉልህ አለመሆኑን (t (46) = .776, p = 0.442) ነው፡፡ በመሆኑም ከነጻ

ናሙናው ትንታኔ በመነሳት የሴት ተማሪዎችና የወንድ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ተመጣጣኝ እንደሆነ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ተችሏል፡፡

የሴት የአማርኛ ቋንቋ ውጤታቸው እና የወንድ ተማሪዎች ውጤታቸው ያለውን ልዩነትም እንዲሁ ፍተሻ ተደርጎበታል፡፡ በዚህም መሰረት በአጥኚው ተዘጋጅቶ ተጠኚ ተማሪዎች ከ50 ነጥብ በተፈተኑት ፈተና 25 ሴት ተማሪዎች ያገኙት አማካይ ውጤት 30.72 ሲሆን የ23 ወንድ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ አማካይ ውጤት ደግሞ 30.00 በመሆኑ የሴት ተማሪዎች ውጤት በ0.72 ውጤት እንደሚበልጥ የሚያሳይ ነው፡፡ የገላጭ ስታትስቲክስ መረጃው ተቀራራቢ እንደሆኑ የሚያሳይ ሲሆን ስታትስቲካዊ ጉልህ መሆናቸውን ለመፈተሽ የነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ ተደርጓል፡፡ በፍተሻው የተገኘው አማካይ ውጤት እንደሚያመለክተው የሴትና የወንድ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት ($t(46) = .301$, $p = .765$) አለመኖሩን ነው፡፡

በቀደምት ጥናቶች ቅኝት እንደተመላከተው በሴትና በወንድ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ በርካታ ጥናቶች የተደረጉ ሲሆን በአብዛኛዎቹ ጥናቶቹ የተገኙ ግኝቶች ግን ከዚህ ጥናት ግኝት ጋር የማይደጋገፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በላይ (1992) የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎን በሚመለከት ባደረጉት ጥናት የተማሪዎችን ተሳትፎ በምልከታና በጽሑፍ መጠይቅ መረጃዎችን ሰብስበው ባደረጉት የትንታኔ ውጤት በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል የተሳትፎ ልዩነት እንዳለ ያመለከቱ ሲሆን ከፍ ያለ ተሳትፎ ያደረጉትም የወንድ ተማሪዎች እንደሆኑ በጥናቱ ተመላክቷል፡፡ በዚህ ጥናት ውጤት የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ሴትና ወንድ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ልዩነት አለመኖሩን በማመልከቱ የውጤት መለያየት ታይቷል፡፡

ለዘር (2004) ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሴቶች ብቻቸውንና ወንዶችና ሴቶች አንድ ላይ በሚማሩባቸው የግል ትምህርትቤቶች የዘጠነኛ ክፍል ሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በንጽጽር ጥናት አድርገዋል፡፡ በጥናታቸው ውጤት ከወንዶች ጋር ተቀላቅለው የተማሩት ሴት ተማሪዎች ያላቸው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ዝቅ ያለ እንደነበር የተገለጸ ሲሆን በዚህ ጥናትም ሴትና ወንድ ተማሪዎች ተቀላቅለው የሚማሩበት ትምህርት ቤት ላይ ጥናት የተደረገ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ግን የተመጣጠነ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ እንዳላቸው ተመልክቷል፡፡ ይህም የለዘር (2004) እና የዚህ ጥናት ውጤት የተለያዩና የማይደጋገፉ

መሆናቸውን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህም መለያየት ሴት ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደቱ ንቁ ተሳትፎ እያደረጉ እንደሆነ የሚያመለክት ነው፡፡

## ማጠቃለያ

የጥናቱን ሶስቱንም መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ መጠናዊ ምርምር ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን ተዛምዷዊ የጥናት ንድፍን ተከትሏል፡፡ ተዛምዶውን ለመፈተሽ በ2015 ዓ.ም. ጊንጪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ 48 የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በጥናቱ ተካተዋል፡፡ ከ48 ተማሪዎች መረጃ የተሰበሰበው በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ ያለ ተሳትፎ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በተደረገ ምልከታ እና በክፍል ውስጥ ተሳትፎ መለኪያ መጠይቅ ነው፡፡ የአማርኛ ቋንቋ ውጤት ደግሞ በአጥኚው በተዘጋጀ ፈተና ተሰብስቧል፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎች በመልክ በመልካቸው በውጤት መመዝገቢያ ሰንጠረዥ ከሰፈሩ በኋላ በገላጭ ስታትትስቲክስ፣ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ፣ በቀላል ድህረት እና በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትነው የሚከተለውን ውጤት አስገኝተዋል፡፡

1. በአማርኛ ቋንቋ ክፍለጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ እና በአማርኛ ቋንቋ ውጤት መካከል ጉልህ የሆነ አዎንታዊ ተዛምዶ ($r=.642$፣ $P<.01$፣ ባለሁለት ጫፍ) እንዳለ የፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ፍተሻው አሳይቷል፡፡ እንደሆነ ያለው (2009) እና Dornyei (2007) ባስቀመጡት መስፈርት መሰረት የተዛምዶ መጠኑ ደግሞ ከፍተኛ እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል፡፡

2. ነጻ ተለዋዋጩ (በአማርኛ ቋንቋ ክፍለጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ) ጥገኛ ተለዋዋጩን (የአማርኛ ቋንቋ ውጤትን) 41.2% እንደሚገልጸው የቀላል ድህረታዊ ትንታኔው ውጤት ($R^2 = .412$፣ $\beta = .642$፣ $F (1፣ 47) = 32.267$፣ $t = 5.680$፣ $p = .000$) አሳይቷል፡፡ ይህም የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በአማርኛ ቋንቋ ውጤት መጨመር ወይም መቀነስ ያለው ተጽዕኖ የላቀ መሆኑን ያሳያል፡፡

3. የወንድና የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ አማካይ ውጤቶች መካከል ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተፈትሾ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል የተገኘው አማካይ ስታትስቲካዊ ጉልህ አለመሆኑን ($t (46) = .776$, $p = 0.442$) ነው፡፡ በመሆኑም ከነጻ ናሙና ቲ-

ቴስቱ ትንታኔ በመነሳት የሴት ተማሪዎችና የወንድ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ተመጣጣኝ እንደሆነ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ተችሏል፡፡

4. የሴት እና የወንድ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ውጤታቸው መካከል ያለውን ልዩነት ተፈትሾ የሴትና የወንድ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አማካይ ውጤቶች መካከል ጉልህ ልዩነት (t (46) = .301, p = .765) አለመኖሩን በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

## አስተያየት

ከጥናቱ ትንታኔና ከጥናቱ ግኝት በመነሳት አጥኚው የሚከተሉትን አስተያየቶች አቅርቧል፡፡

1. በጥናቱ ግኝት እንደተመላከተው በአማርኛ ክፍለ ጊዜ የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ያላቸው ተዛምዶ ጉልህ የሆነ አዎንታዊ ነው፡፡ የተዛምዶ መጠናቸውም ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም መምህራን የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ እንዲጨምር የበኩላቸውን አስተዋጽዖ ቢያበረክቱ፤

2. በጥናቱ ግኝት መሰረት እንደተገለጸው የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የአማርኛ ትምህርት ውጤታቸውን የመተንበይ ድርሻው ከፍተኛ ነው፡፡ ይህም የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ውጤት ከፍ እንዲል ለማድረግ የክፍል ውስጥ ተሳትፎን ከፍ ማድረግ ያለው አስተዋጽዖ ከፍ ያደርጋል የሚል አንድምታ አለው፡፡ በመሆኑም መምህራን የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል ተማሪዎችም እንዲሳተፉ በማነቃቃትና አሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴዎችን በመከተል ተሳትፏቸውን እንዲጨምር ቢያደርጉ፤

3. የክፍል ውስጥ ተሳትፎ እና የትምህርት ውጤት ካላቸው ከፍተኛ ዝምድና አንጻር ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፏቸውን በማሳደግ ውጤታቸውን ማሳደግ እንዲችሉ የሥርዓተ ትምህርት አዘጋጆች መማሪያ መጻሕፍትንና የመምህር መምሪያዎችን ሲያዘጋጁ ተማሪዎች እንዲሳተፉ ምቹ የሆነና የሚያበረታታ እንዲሆን ትኩረት ቢያደርጉ፤

4. በጥናቱ ግኝት እንደተገለጸው የሴትና የወንድ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎም ሆነ በአማርኛ ትምህርት ውጤታቸው ተመጣጣኝ ናቸው፡፡ ሆኖም በቀደምት ጥናቶች ቅኝት እንደተገለጸው፣ በጥናቱ ማብራሪያ ላይም እንደተብራራው የሴት ተማሪዎች የክፍል

ውስጥ ተሳትፎ ከወንዶች ያነሰ ነበር፡፡ በዚህ ጥናት ውጤት ግን የተመጣጠነ በመሆኑ በሁለቱም ጾታዎች ያለው የተሳትፎ ምጥጥን ተጠናክሮ እንዲቀጥል ቢደረግ፡፡

## ዋቢዎች


ለዘር አሊ፡፡ (2004)፡፡ "በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሴቶች ብቻቸውንና ወንዶችና ሴቶች አንድ ላይ በሚማሩባቸው የግል ትምህርትቤቶች የዘጠነኛ ክፍል ሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ንጽጽራዊ ጥናት"፡፡ አማርኛን ለማስተማር የማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

በላይ ሰይድ፡፡ (1992)፡፡ "የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ፤ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት"፡፡ አማርኛን ለማስተማር የማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ኤርምያስ ጥላሁን፡፡ (1996)፡፡ *በትምህርት ስኬታማነትን የሚያጎናጽፉ መርሆዎች፡፡* አዲስ አበባ፤ ብራና ማተሚያ ድርጅት ታተመ፡፡

ግዛቸው አግማሴ፡፡ (2014)፡፡ "ስነፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበርና የተማሪዎች ተሳትፎ ተዛምዷዊ ጥናት (በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)"፡፡ አማርኛን ለማስተማር የማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

Amidon, E. J. (1976). *The Role of the Teacher in the Classroom: A manual for understanding and improving teachers' classroom behavior*. Association for Productive Teaching. New York.

Borich, D. G. (2004). *Effective Teaching methods.* 5th Edition. pearson Education Ltd.

Dornyei, Z. (2007). *Research Methods in Applied Linguistic*. Oxford: OPU.

Eggen, P. D, & Kauchak, D. P. (2013). *Educational Psychology: Windows on Classrooms*. (Ninth Edition). Peason Education, Inc.

Evertson, C. M., Anderson, C. W., Anderson, L. M., & Brophy, J. E. (1980). Relationships Between Classroom Behaviors and Student Outcomes in

Junior High Mathematics and English Classes. American Educational Research Journal, 17(1), 43—60. https://doi.org/10.3102/00028312017001043

Kauchalk, P. D. (1993). Learning and Teaching. 2nd Edition. U.S.A. Library of congress cataloging in Publication data.

Marx, M. H. & Marion, E. B. (1977*). Fundamentals and applications of Learing*. Newyork: Macmillan pulishing Co. Inc.

Nichols, R. C. (1978). Policy Implications of the IQ Controversy. *Review of Research in Education*, 6(1), 3-46.

Richards, J.C. (2001) Curriculum Development in Language Teaching. CUP, Cambridge. https://doi.org/10.1017/CBO9780511667220

Skinner, E. C. (1985). *Educational psychology*. (4th edition). Prentice Hall. Inc. Englewood Clifts. N.J.

Slavin, R. E. (2018). *Educational Psychology*: *Theory and Practice*. (10th Edition). pearson Education Ltd.

Stevenson, J. S. & Joy, A. P (1994). *Learning principles, processes and practices.* Cassell Educational Limited.

Tony, W. (1987). Role of Teachers and Learners. Oxford: Oxford University Press.

Tudor, L. (1993). Teacher Roles in the Learner-Centered Classroom. *ELT Journal,* 47 (1), 22-31.